እዉነት አማርኛ የአማራዉ ቋንቋ ነዉን ?

መልሱ አዎን ነዉ ከተባለ፣

ታዲያ ለምንድን ነዉ? የሚከተሉትን መለስ የተናገራቸዉን ዓረፍተ ነገሮች/አንቀጾችአማራዉ መረዳት የአቃተዉ፡፡

በ1997ዓ.ም መለስ ሥልጣን ለምን? ለቅንጅት አታሰረክቡም ተብሎ ሲጠየቅ “እኛ ሥልጣን ለአማራዉ አንሰጥም ፡፡”

ቅንጅት እኮ የአማራ ድርጅት አይደለም ፡፡ትግሬዎችም አሉበት ሲባል “ናዚዉስጥም አይሁዶች ነበሩበት፤”

የአሜሪካዉ ዲፐሎማት ኸርማንኮን መሬት የግልህብት ለምን? አይሆንም ብለዉ ሲጠይቁት “መሬት በአማራዉ እጅ ይገባና ወደ ነበረበት የጢሰኝነት ሥርዓት የገባል።”

ኤርትራ የመጀመሪያዉ ጉባኤ ላይ ተገኝቶ ንግግር ሲያደርግ “ቁስል እንዳለባችሁ አዉቃለሁ: ለምን? ብትሉ በጀርባችሁ ያለዉ ቁስል በኔም ጀርባ አለ። ይህን የአለፈዉን ምእራፍ እርሱት አልላችሁም ነገር ግን አልፏል ከፉ ከፉዉን ቀብረነዋል ፡፡”

በኤርትራ የነፃነት ቀን አስመራ ተገኝቶ “የህወሀት እምነት የመሪዎች እምነት የኤርትራ ጉዳይ የቅኝ ግዛት ጥያቄ ነዉ።”

ለኢትዮጵያ ፓርላማ ተብየዉ ስለደንበሩ ሲናገር “የእኔን ለእኔ የእናንተን እን ካፈል የሚለዉን የተስፋፊነት አቋምን ችሎ በአደረ፤ የሱዳን መንግሥት እንደ እንዝላል ሊቆጠር አይገባም ።እንደአስተዋይ እንጂ፤ በ1996ዓም የኢትዮጵያ ጦር ሂዶ የያዘዉን መሬትነዉ የሰጠናቸዉ የተፈናቀለየለም፡፡”

የነፃትምህርት እድል 100 ፐሰንት ለትግራይ ይሰጣል ተብሎ ሲጠየቅ “አማራዉ ቀድሞ ስለተማረ ነዉ። ለትምክህተኛ አማራ ሥልጣን አንለቅም።”

“የነፍጠኛዉ ተረትና ታሪክ የኢትዮጵያ ህዘቦች በሙሉ አድርገዉ ነዉ፣ የሚተርኩት የተዋረደዉን ታሪካችን በአዲስ መልክ እንመሰርታለን፡፡” አንተም በሚል ርዕስገጽ 12እስከ13 ጋዜጠኛዉ ሲጠይቅ ቁጥራቸዉ ቀላል የማይባል ኢትዮጵያዊ አሰብ የኢትዮጵያ አካል ናት ይላሉ፤ብሎ ሲጠይቀዉ “እነዚህ ህልመኞች ናቸዉ። አሰብ የኤርትራ እንጅ የኢትዮጵያ አይደለችም፡ ፡ እንዲያዉም እስከአሁን የተጠቀማችሁበትን ሂሳብ ወደኋላ ተመልሰን እንጠይቃለን ነዉ፤ የአሉት፡፡”

ደጃዝማች አመባሳደር ዘዉዴ ገብረሥላሴ የክንፈ አብርሃን ቦታ እንዲይዙ ሲጠየቁ ለምን? ትግሬንብቻ ተሸማለህ ቁጥሩ ትንሽ ነዉ ሲሉት “አሰቤበት ነ ዉ የምሰራዉ የአይሁዶችን ታሪክ ይመልከቱ የትግሬን ተወላጅ በኢኮኖሚ በማጠንከርና ባህላቸዉን በማስፋፋት ለረጂም ጊዜ በሥልጣን እንዲቆዩ አደርጋለሁ፡፡”

“በአማራዉ ላይ የዘመተዉ አማራ ነን የሚሉትም ሌሎችም በአማራዉ ላይ የዘመተነዉ ስንል  የአለፉት የቅርብና የሩቅ ጊዜ አፄዎች በሰጡነ አትዮጵያ ላይ ነዉ፡፡”

“አንድ ሰዉ መንገድ ልማዉጣት ደን የሚመነጥረዉ ከደኑ ጋር ጠላትነት የአወጀዉ አላስኬድ አላሳልፍ ስለአለዉ ነዉ፡፡”

“ዘመን ተሸሮ ዘመን በተተካ ቁጥር፤ መብትን ለራሳቸዉ እየቸሩ ሰፊዉን ህዝብ ሲረግጡእና ሲመዘብሩ የኖሩ፤ አምባ ገነን መንግሥታት በሰላም ያለቀቁልነን መብታችን ብትግላችን አምበረከክናቸዉ፡፡ የተሰነዘሩትን የባርነት ሰንሰለት  እንዴት እንደበጣጠስነዉና ዲሞክራሲን ከወህኒቤት እግረሙቅ አላቀን ከእዉነተኞች ባለመብቶች ጋር እንዴት እነዳገናኘናት እኛም እነሱም በህወት እያለን አሳይተናቸዋል፡፡”

“አማራዎች ሲመነጠሩ ሌላዉ ኢትዮጵዊ የሚቆጣዉ ኢትዮጵያን የማፍረሱ ዓላማ ሲፈጸም ወለል ብሎ ስለታያቸዉ እንጂ አማራ ስለሆኑና ለአማራዉ አድልተዉ እንዳልሆነ አማራዉ ይረዳል፡፡”

አማራዉ ከሌሎች ክልል ሲፈናቀል ለምንድን ነዉ? ተብሎ ሲጠየቅ "አማራዉ የሌላዉን ባህል ይበርዛል የሌላዉን መሬት በመዉረስ ነፍጠኝነትን ያስፋፋል፡፡"

"በብሄራዊ ጥያቄ ዙሪያ አቋምን ተጠቅመን ከሌሎች ጋር በመተባበር አማራን ለማጥፋት አቀድን::"

"አማራና ኢፔሪያሊዝም የትግራይ ቀንደኛ ጠላቶች ናቸዉ፡፡"

"በአንድ የፖለቲካ መዋቅር ሥር አማሮችና ሌሎች በሄረሰቦችን የአካተተ የተቀናጀ የመደብ ትግል ስኬት አይኖረዉም፡፡"

" የአፄ ቴዎድሮስ መድፍ መስራት ተራጀዲ/አሰቃቂ ነዉ፡፡"

" አፄ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን አንድ ማድረጋቸዉ የጦርነት ስራ ነዉ፡፡''

" አማሮች በፖለቲካም ሆነ በሌላ አኳኋን የቅርብ ትስስር የለላቸዉ ቡደኑች ናቸዉ፡፡"

"መሬት መሸጥ መለወጥ የሚቻለዉ በኢህአዴግ መቃብር ላይ ብቻነዉ፡፡"

ሰላሳ ዓመት በሙሉ በኤርትራ ዉስጥ ፍጥረት ሲጋይና ሲከስል፣ የቤተሰብ መብት እና ንብረት መዉደሚያ ሁኖ የኖረዉ የኤርትራ ጦርነት፣ በአማራዉ ነፍጠኝነት በመሆኑ አማራዉ ይቅርታ ይጠይቃል፣ ካሳም ይከፍላል፣ ተብሎ ካሳዉ በአሰብና በምፅዋ የነበረዉ የኢትዮጵያ ንብርት በሙሉ ለኤርትራዊያን ሲሰጥ ይቅርታዉ ፕሮፌሰር ተብየዉ በእንድሪያስ አሸቴ አራጋቢና አጦንጢኝነት ከጎጃም

1.አቶ ዮሐንስ መሀሪ በደርግ ጊዜ የቢቸና አስተዳዳሪ የነበረ ተመልሶ ከተኛበት አለጋ ላይ ሞቶ የተገኘ፤

2.መምህር ምናሌ መብራቴ የደብረማረቆስ ከፍተኛ ሁለተኛ አጠቃላይ ትምህርትቤት መምህር ተመልሶ ከተኛበት አልጋ ላይ ሙቶ የተገኘ፤
3.መምህር ዮሴፍ ለይኩን ሲመለስ ምላሱን ተቆረጦ የሞተ፤ በነዚህ ተወካይነት አማራዉ ይቅርታ እንዲጠይቅ ተደርጓል፡፡

አንባቢያን በሙሉ በተለይ አማራነኝ የምትሉ፣ ይህ ጽሁፍ በአሁኑ ጊዜ ሊቅርብ የቻለበት ምክንያት መለስ አማራን ለማጥፋት ሲነሳ ዓላማዉን ያቅደበት ፣ የአፈጻጸም ስልቱን የነደፈበት እና ፅንሰ ሃሳቦቹን ያሰተላለፈባቸዉ አረፍተ ነገሮችና አንቀጾች፣ መለስ ሳለም የሰራባቸዉ ሲሞተም በኑዛዜ እድሜ ልክ እንዲሰራባቸዉ ያስተላለፋቸዉ፣ የመለስ ሌጋሲ በሚል ስያሜ እየተሰራባቸዉ ያሉና የሚኖሩ እንጂ ከመለሰ ጋር የተቀበሩ አለመሆናቸዉን አማራዉ አዉቆ እራሱን አደራጅቶ የመለስን ሌጋሲ ለማጥፋት እነደቧንቧ የሚያገለግሉትን ማጥፋት እነዳለበት እነዳይዘናጋ የእለት ከእለት ተዉስታ እነዲኖረዉ በሚል ነዉ፡፡ የተከታዩን በሚቀጥለዉ አቀረባለሁ፡፡

ከቀስቅስ